የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
MINISTRY OF CIVIL SERVICE

ቁጥር ሲሰሚ/...
Ref. No.

ቀን 28 ግንቦት 2007
Date

ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኒካል ረዳቶች የሙያ ዕድገት ተኳሂዶ መሰላል /Carear Structure/ ማሻሻል አስመልክቶ ባቀረበው ጥያቄ ጥናት ተካሂዶ በቁጥር መ/90-813/5 በተፃፈ ደብዳቤ አስተያየት እንዲቀርብ ግንቦት 11 ቀን 2006 ዓ.ም መታዘዙ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ትምህርት ሚኒስቴር ያቀረበውን ጥያቄ መነሻ በማድረግ ለቀረበው ጥያቄ የትምህርት ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲቀርብ በማድረግ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የትምህርት ሚኒስቴር ባለሙያዎች ጋር ውይይት ከተደረገ በኋላ ተገቢው ማስተካከያ ተደርጎበት የተዘጋጀውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኒካል ረዳቶች የሙያ ዕድገት መሰላል አስተያየት ለውሳኔ ማቅረባችንን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
ለአደረጃጀት ሥራ ምዘናና የክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት
ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ፣

ስልክ:- 011-554 96 66 /67/68
Tel.
ፋክስ:- 011-552 55 61
Fax:- 011 552 73 79
E-Mail:- mocis@ethionet.et
Website:- www.mocis.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. 1082
P.O.Box:
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ድህነትን ለማሸነፍ ማገልገል ድርብ ክብር ነው!

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ መነሻ

የዚህ ጥናት መነሻ የትምህርት ሚኒስቴር ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኒካል ረዳቶች ባቀረበው የዕድገት መሰላል /Career Structure/የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጥበት ግንቦት 11 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር መ/90-813/5 በተጻፈ ደብዳቤ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ነው።

### 1.2 የጥናቱ ስልት

- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር የቀረበውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኒካል ረዳቶች የዕድገት መሰላል አጥንቶ አስተያየት እንዲያቀርብ በታዘዘው መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ልዩ ልዩ መረጃዎች ፈትሿል። እነርሱም፦

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በአዳማና በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች ለሚያገለግሉ የምርምር ረዳቶች የተፈቀደው የዕድገት መሰላልና የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ፣

- ትምህርት ሚኒስቴር የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የቴክኒካል ረዳቶች የዕድገት መሰላል ለማሻሻል ያቀረበውን ጥናት፣
- የትምህርት ሚኒስቴር ስለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኒካል ረዳቶች የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ፃ/1-1/297/641/35 በተጻፈ ደብዳቤ ያቀረበው ተጨማሪ ማብራሪያ እና
- አሁን በሥራ ላይ ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቴክኒካል ረዳቶች የእድገት መሰላል፣

ናቸው።

በተጨማሪም ከትምህርት ሚኒስቴር የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ ከሰነዶች ፍተሻና ከውይይት የተገኙ ሃሳቦች እንደ አግባብነታቸው ለጥናቱ ማዳበሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል

## 2. ዝርዝር ጥናት

### 2.1 የቴክኒክ ረዳቶች የደመወዝ ስኬል

በሥራ ላይ ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኒካል ረዳቶች 3 የዕድገት መሰላል ያላቸው ሲሆን፣ ዝቅተኛው ደረጃ I ብር 1663 የመነሻ እና ብር 2628 የመድረሻ ደመወዝ ያለው፣ የከፍተኛ ደረጃ III ደግሞ ብር 2897 የመነሻ እና ብር 3425 የመድረሻ ደመወዝ ያለው ነው። ሶስቱ ተዋረዶች የሚጠይቁት ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ የኮሌጅ ዲፕሎማ ነው ። የደመወዝ ስኬሉ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

በሥራ ላይ ያለ የዩኒቨርስቲ ቴክኒክ ረዳቶች የደመወዝ ስኬል

(ሐምሌ 2006 ዓ.ም)

| ደረጃ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | መነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዝ | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| I | ቴክኒካል አስሲታንት I | 1663 | 1743 | 1828 | 1916 | 2008 | 2100 | 2197 | 2298 | 2404 | 2514 | 2628 |
| II | ቴክኒካል አስሲታንት II | 1916 | 2008 | 2100 | 2197 | 2298 | 2404 | 2514 | 2628 | 2748 | 2872 | 3001 |
| III | ቴክኒካል አስሲታንት III | 2197 | 2298 | 2404 | 2514 | 2628 | 2748 | 2872 | 3001 | 3137 | 3278 | 3425 |

### 2.2 የቴክኒካል ረዳቶችን የዕድገት መሰላል ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት

በሣይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች ላይ ያተኮረው የከፍተኛ ትምህርት ስራ የተግባር ትምህርትን ስለሚያካትት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን የጽንሰ ሃሳብ ትምህርት በላቦራቶሪዎች ውስጥ በቴክኒካል ረዳቶች ድጋፍ ተግባራዊ ልምምድ እንዲያገኙ ይደረጋል።

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Education Mizan-Tepi University
The Federal Democratic Republic of Ethiopia MINISTRY OF CIVIL SERVICE

የአካዳሚክ ባለሙያዎች ጥናትና ምርምር ሥራ ሲያካሂዱም የቴክኒካል ረዳቶች ድጋፍ ያደርጋሉ። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሳይንሳዊ መሣሪያዎች እየረቀቁ መምጣት ከቀድሞው የተሻለ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያለው ባለሙያ ለሥራው አስፈላጊ እየሆነ መምጣቱን መገንዘብ ተችሏል።

## 2.3 የቀረበው የቴክኒካል ረዳቶች የዕድገት መሰላል

በዚህ የጥናት የቀረበው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቴክኒካል ረዳቶች እያንዳንዳቸው በሶስት ተዋረድ ያለው የቴክኒካል ረዳት፣ ሲንየር የቴክኒካል ረዳት እና ችፍ ቴክኒካል ረዳት ተብለው የተከፈሉ ናቸው። የመጀመሪያው የቴክኒካል ረዳት ሶስት ተዋረዶች የኮሌጅ ዲፕሎማ የሲንየር ቴክኒካል ረዳት ሶስት ተዋረዶች የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም የችፍ ቴክኒካል ረዳት ሶስት ተዋረዶች የ2ኛ ዲግሪ የሚጠይቁ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል። ዝርዝራቸውም ፦

- ቴክኒካል ረዳት I
- ቴክኒካል ረዳት II - 2005 -
- ቴክኒካል ረዳት III - 2005 -
- ሲኒየር ቴክኒካል ረዳት I - 2007 - ?
- ሲኒየር ቴክኒካል ረዳት II - 2009 -
- ሲኒየር ቴክኒካል ረዳት III
- ቺፍ ቴክኒካል ረዳት I
- ቺፍ ቴክኒካል ረዳት II
- ቺፍ ቴክኒካል ረዳት III

ናቸው።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia MINISTRY OF CIVIL SERVICE

## 2.4 በጥናት ሰነዱ የቀረበው የቴክኒካል ረዳቶች የዕድገት መሰላልን በተመለከተ

አዲስ የቀረበው የቴክኒካል ረዳቶች ደረጃና ያመወዝ ከሌሎች የአካዳሚክ ሙያዎች ጋር ሲታይ በአቻነት እስከ ፕሮፌሰር የሚደርስ መሆኑ ከቀረበው ሰነድ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ ለሙያዎች የቀረቡ መስፈርቶች ግን ከአካዳሚክ ሙያተኞቹ በጣም የላሉና ዝቅ ያሉ ናቸው።

የቴክኒክ ረዳቶች የዕድገት መሰላል ሲፈጠር የነበረው አስተሳሰብ ጥሩ የአካዳሚክ ችሎታ ያላቸው የዲፕሎማ ምሩቃን እየተመለመሉ ከዩኒቨርስቲ የአካዳሚክ ባለሙያዎች (መምህራን) ለተማሪዎች የሚሰጡ የተግባር ሙከራዎች ሲኖሩ ተማሪዎችን ተግባራዊ ድጋፍ በመስጠት እንዲያገለግሉ፣ የአካዳሚክ ሙያተኞች ጥናትና ምርምር ሲያካሂዱም የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ በመፈፀም ድጋፍ እንዲሰጡ ለማድረግ ነው።

- በሂደትም የቴክኒክ ረዳቶቹ ራሳቸውን በከፍተኛ በትምህርት በማዳበር የአካዳሚክ ዘርፉን በሙሉ ኃይል እንዲቀላቀሉ ለማገዝ ነበር። ሆኖም አንዳንድ የቴክኒክ ረዳቶች ከፍተኛ ትምህርት ሲቀጥሉ ለአካዳሚክ ሙያተኛነት የተቀመጠ ዝቅተኛ የመግቢያ ነጥብ (2.75) ማምጣት ባለመቻላቸው የመጀመሪያም ሆነ የ2ኛ ዲግሪ ቢኖራቸውም ነባር የቴክኒክ ረዳት ደረጃቸውን እንደያዙ ቀጥለዋል።

- እስካሁን በነበረው አሠራር የእነዚህ ቴክኒካል ረዳቶች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ዲፕሎማ ቢሆንም ዩኒቨርስቲዎች አሁን ከደረሱበት የእድገት ደረጃ አንፃር ለተማሪዎችም ሆነ የጥናትና የምርምር ሥራ የሚያከናውኑ የአካዳሚክ ሙያተኞች በዚህ ሙያ የመጀመሪያና የ2ኛ ዲግሪ ትምህርት ደረጃ ያለው ባለሙያ አስፈላጊ እየሆነ መምጣቱን በጉዳዩ ላይ ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር ከተደረገ ውይይት መገንዘብ ተችሏል።

በተደረገ የሰነድ ፍተሻ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለአዳማና ለአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያጠናቀቁ አራት ተዋረድ ያላቸው የቴክኒክ ረዳት ሥራ መደቦች መፈቀዱን መገንዘብ ተችሏል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia MINISTRY OF CIVIL SERVICE

እነርሱም :-

- የአካዳሚክና ምርምር ረዳት ትምህርት ደረጃ - ደረጃ III ወይም ደረጃ IV፣
- ሲኒየር የአካዳሚክና ምርምር ረዳት ትምህርት ደረጃ - የመጀመሪያ ዲግሪ፣
- ችፍ አካዳሚክና ምርምር ረዳት ትምህርት ደረጃ - 2ኛ ዲግሪ እና
- ችፍ አካዳሚክና ምርምር ረዳት ትምህርት ደረጃ - 2ኛ ዲግሪ፣

የሚጠይቁ ናቸው።

ይህ አራት ተዋረድ ያለው የምርምር ወይም የቴክኒካል ረዳት በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ቢተገበር :-

- አንድ ወጥ አሠራርን በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ለማስፈን ስለሚያስችል፣
- የቴክኒካል ረዳት ሥራ እንደየሥራ ባህርይው ከዲፕሎማ እስከ 2ኛ ዲግሪ ችሎታ ያላቸው ሙያተኞች እንዲመደቡበት መደረጉ ለተግባር ልምምድ ተማሪዎች ጥራት ያለው አገልግሎት ለማበርከት ስለሚረዳ፣
- በቴክኒካል ረዳትነት ተቀጥረው ትምህርታቸውን በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ዲግሪ ላሻሻሉ ሙያተኞች ተጨማሪ የዕድገት መሰላል በመፍጠር ተረጋግተው እንዲሠሩ ስለሚያስችል፣
- የቴክኒካል ረዳት የሥራ መደቦች ከቀድሞው በተሻለ ሁኔታ እስከ 2ኛ ዲግሪ ባሉ ሙያተኞች እንዲሸፈን መደረጉ ከፍ ያለ የጥናትና ምርምር የሚያካሂዱ የአካዳሚክ ሙያተኞች ፍላጎታቸውን በግልጽ ተረድቶ የላቀ አገልግሎት ሊሰጣቸው የሚችል ረዳት ሙያተኛ ስለሚያስገኝላቸው፣
- ቴክኒካል ረዳቶች፣ ችሎታቸውን በከፍተኛ ትምህርት እያዳበሩ ረዘም ላለ ጊዜ በመስኩ ተሰማርተው እንዲያገለግሉ ስለሚረዳ፣
- በመዘጋጀት ላይ ባለው የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ፕሮጀክት ጥናት በሥራ መደቦች መካከል ያለውን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ለመለየትና የሥራ መደቦችን ተዋረድ በአሪት ተዋረድ እንዲሰባሰቡ ከተዘረጋው ጋር ለማጣጣም ስለሚጠቅም፣

ከምርው ጋር ተገናዝቧል
ፊርማ L615/10

- ለአዲስ አበባ እና ለአዳማ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች የተፈቀደው ባለአራት የዕድገት መሰላል የቴክኒክ ረዳት የዕድገት መሰላል ለሁሉም ዩኒቨርስቲዎች እንዲፈቀድ አስተያየት ቀርቧል። ከዚህ በላይ የቀረበው አስተያየት ተቀባይነት እንደሚያገኝ በማመን የሚመለከተው የደመወዝ ስኬል ለቴክኒክ ረዳቶች ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

## 2.5 የደመወዝ ስኬል

አራት የዕድገት መሰላል ላላቸው ቴክኒካል ረዳት የሥራ መደቦች ቀደም ሲል ለአዲስ አበባ እና ለአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች የምርምር ረዳቶች ተፈቅዶ የነበረው የደመወዝ ስኬል የዝቅተኛ ደረጃ I መነሻ ደመወዝ 2495 ሲሆን መድረሻው 4702 የከፍተኛ ደረጃው የመነሻ ደመወዝ ብር 5200 መድረሻው ብር 8495 ነው ። የደመወዝ ስኬሉ እንደሚከተለው ቀርቧል።

**የቴክኒካል ረዳቶች የዕድገት መሰላልና የደመወዝ ስኬል**

| ደረጃ | የሥራ መደብ | መነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዞች | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| I | ቴክኒካል ረዳት | 2495 | 2675 | 2856 | 3037 | 3217 | 3464 | 3711 | 3958 | 4205 | 4454 | 4702 |
| II | ሲኒየር ቴክኒካል ረዳት | 3217 | 3464 | 3711 | 3958 | 4205 | 4454 | 4702 | 4951 | 5200 | 5455 | 5710 |
| III | ችፍ ቴክኒካል ረዳት I | 4205 | 4454 | 4702 | 4951 | 5200 | 5455 | 5710 | 5965 | 6220 | 6495 | 6795 |
| IV | ችፍ ቴክኒካል ረዳት II | 5200 | 5455 | 5710 | 5965 | 6220 | 6495 | 6795 | 7145 | 7545 | 7995 | 8495 |

3464
4454
3464
30

## 2.6 ተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ

ቴክኒካል ረዳት የሥራ መደቦች በሰስት ደረጃዎች ተከፍለው :-

- ዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ ያለው በደረጃ I እና II፣
- ከፍተኛ ኮሌጅ ዲፕሎማ ትምህርት ያለው በደረጃ I፣ II እና III እና
- የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያለው በደረጃ II እና III እንዲሁም
- የሁለተኛ ዲግሪ ያለው ሠራተኛ በደረጃ III እና IV ላይ አገልግሎት እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

ለእያንዳንዱ የዕድገት መሰላል ዝቅ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ [illegible]ሚገባውን የአገልግሎት ዘመንና ለሁለቱ ከፍተኛ የሥራ መደቦች (ችፍ ቴክኒካል ረዳቶች I እና II . በታዋቂ ባለሙያ የተመሰከረለት የላብራቶሪ ማንዋል ማዘጋጀትን ይጠይቃል። የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያው ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

## የቴክኒካል ረዳቶች የሥራ መደቦች የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ

| ደረጃ | ደመወዝ | የሥራ መደብ መጠሪያ | የትምህርት ደረጃ | የሥራ ልምድ/ችሎታ /በዓመት/ |
|---|---|---|---|---|
| I (X) | 2495 | ቴክኒካል ረዳት | 10+3 ወይም ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III<br>ወይም<br>ከፍተኛ ኮሌጅ ወይም ዲፕሎማ ወይም ደረጃ IV | 2<br><br>0 |
| XII | 3217 | ሲኒየር ቴክኒካል ረዳት | 10+3 ወይም ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III<br>ወይም<br>ከፍተኛ ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ IV<br>ወይም<br>የመጀመሪያ ዲግሪ | በቴክኒካል ረዳትነት 3 ዓመት የሥራ<br><br>በቴክኒካል ረዳትነት 2 ዓመት የሥራ<br><br>0 |
| III (XIV) | 4205 | ችፍ ቴክኒካል ረዳት I | ከፍተኛ ኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ IV<br>ወይም<br>የመጀመሪያ ዲግሪ<br>ወይም<br>2ኛ ዲግሪ | በሲኒየር ቴክኒካል ረዳትነት 3 ዓመት የሥራ<br><br>2 ዓመት በሲኒየር በቴክኒካል ረዳትነት የሥራ ሁለት የላቦራቶሪ ማንዋል ያሳተመና በታወቁ ባለሙያ የተረጋገጠ<br><br>0 |
| IV (XVI) | 5200 | ችፍ ቴክኒካል ረዳት II | 2ኛ ዲግሪ | በችፍ ቴክኒካል ረዳት I ደረጃ 2 ዓመት የሥራ፣ ሁለት የላቦራቶሪ ማንዋል ያሳተመና በታወቀ ባለሙያ የተረጋገጠ |

## 3. የአፈጻጸም መመሪያ

ይህ መመሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ሲሆን በሥራ ላይ ካሉ ሠራተኞች መካከል፡-

3.1 የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III ሆኖ እስከ አምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ደረጃ I ላይ ይደለደላሉ::

3.2 የትምህርት ደረጃቸው ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያላቸው ደረጃ II ላይ ይደለደላሉ::

3.3 የትምህርት ደረጃቸው ከፍተኛ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ IV ሆኖ እስከ አምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ደረጃ I ላይ ይደለደላሉ::

3.4 የትምህርት ደረጃቸው ከፍተኛ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም ደረጃ IV ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ያላቸው ደረጃ II ላይ ይደለደላሉ::

3.5 የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ደረጃ II ላይ ይደለደላሉ::

3.6 የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ደረጃ III ላይ ይደለደላሉ::

3.7 ቴክኒካል ረዳቶች የተመደቡበትን ደረጃ የመነሻ ደመወዝ ደርሰውበት ወይም አልፈውት ከሆነና ደመወዛቸው በሁለት የዕርከን ደመወዞች መካከል ካረፈ በቅድሚያ ደመወዛቸው አቅራቢያው ወዳለ ከፍ ያለ የእርከን ደመወዝ ላይ እንዲያርፍ ከተደረገ በኋላ የአንድ እርከን ጭማሪ እንዲሰጣቸው ይደረጋል::

# የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ

# የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናት፣ አፈቃቀድ እና አፈፃፀም መመሪያ

ነሐሴ 2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ከዋናው ጋር ተገናዝቧል.
16/05/2010